# የጥፋት መንገደኞችን እርቃን ያስቀረ እውነት!

ዳዊት አጥናፉ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰሞኑን ኢትዮጵያን ጨምሮ 18 አገራትን የድርጅቱ የሰብአዊ መብት ጉዳዮች ምክር ቤት አባል አድርጎ መርጧል፡፡ ምክር ቤቱ የመረጣቸው እነዚህ አገራት የሚያገለግሉት ለሶስት ዓመታት ሲሆን ከአፍሪካ የተመረጡት ኢትዮጵያን ጨምሮ አምስት አገራት ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ጥበቃ ምክር ቤት ዋነኛ ኃላፊነት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚታዩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተግባራትን በመከታተል ተገቢ የሆነ የእርምት እርምጃ ይወሰድ ዘንድ ለከፍተኛው የድርጅቱ አካል የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ጉዳይ በአባል አገራት ዘንድ ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግም የምክር ቤቱ ተግባር ነው፡፡

በመሆኑም የምክር ቤቱ አባላት ለሰብአዊ መብት ጉዳይ የሚቆረቆሩና የሰዎችን ሁለንተናዊ መብቶች ለማስከበር ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያላቸው ሊሆኑ እንደሚገባ መገመት አያዳግትም፡፡

የተመድ ሰብአዊ መብት ጥበቃ ምክር ቤት አባላቱን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ተቆርቋሪ ነን የሚሉ አካለትና አንዳንድ የአገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ሰዎች የተለያዩ ትችት ሰንዝረዋል፡፡ የእነዚህ አካላት ዋነኛው ትችት ኢትዮጵያን ጨምሮ ምክር ቤቱ ውስጥ በአባልነት የተካተቱት አንዳንድ አገራት በሰብአዊ መብት ጥበቃ መልካም ስም የሌላቸው በመሆኑ ለኃላፊነቱ ብቁ አይደሉም የሚል ነው፡፡

እንደ እኔ ምልከታ ይህ የተሳሳተና ግዙፉን ዓለም አቀፍ ድርጅት የማይረባ አድርጎ መመልከት ነው፡፡ ምክንያቱም በተቋቋመበት ቻርተር ውስጥ ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው የደርጅቱ ግቦች መካከል አንዱና ምናልባትም ቁልፍ የሚባለው የሰው ልጅ ሰብአዊ መብት የሚገባውን ክብርና ጥበቃ እንዲያገኝ አስፈላጊውን

እርምጃ መውሰድ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ እንከን የሌለውና የተዋጣለት ነው ብሎ መናገር ባይቻልም ይህንን ዓላማውን ለማስፈፀም ድርጅቱ የተለያዩ ተቋማትን መስርቷል፤ ልዩ ልዩ ተግባራትንም በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ከእነዚህ የመንግስታቱ ድርጅት ተቋማት መካከል አሁን ኢትዮጵያ በአባልነት እንድታገለግል የተመረጠችበት ምክር ቤት የተመሰረተው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ 2006 ነው፡፡ ከዚህ በፊት የሰብአዊ ጉዳዮችን ይከታተል የነበረው የተመድ አካል የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በመባል የሚጠራ ነበር፡፡

በዚህ ኮሚሽን ውስጥ አገራት የሚወከሉት በኮታና በተራ በመሆኑ በሰብአዊ መብት ጥሰት ከፍተኛ ወቀሳ የሚሰነዘርባቸው አገራት ጭምር የኮሚሽኑ አባል የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ እንደነበር ከመንግስታቱ ድርጅት የወጣ አንድ ሰነድ ይገልፃል፡፡

በዚህም የተነሳ ኮሚሽኑ የተጣለበትን ታላቅ ዓለም አቀፍ ኃላፊነት በብቃት መወጣት አልቻለም የሚል ወቀሳ ከየአቅጣጫው ይቀርብበት ነበር፡፡ የአሁኑ የሰብአዊ መብት ምክር ቤት የተቋቋመውም ይህንን ችግር በማስወገድ አገራት ለሰብአዊ መብት ጥበቃ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

በዚህ ምክር ቤት ውስጥ አባል ሆነው የሚያገለግሉ አገራት በሰብአዊ መብት ጥበቃ ጉዳይ የማይታሙና የሰብአዊ መብት ጥበቃን ለማጠናከርም ወሳኝ የሆኑ እርምጃዎችን የሚወስዱ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ እንደሆነም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ከተመሰረተ ስድስት ዓመታትን ያስቆጠረው የዚህ ምክር ቤት አባል አገራት የሚሰየሙት እንደበፊቱ በኮታና በተራ ሳይሆን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በሚያካሄደው ቀጥታ ምርጫ አብላጫ ድምፅ ያገኙት ናቸው፡፡ ምርጫው ከመካሄዱ በፊትም በምክር ቤቱ አባል በመሆን ለማገልገል ፍቃደኛ የሆኑ አገራት የሰብአዊ መብት ጥበቃ አጠቃላይ ሁኔታም በጥልቀት ይመረመራል፡፡ ይህ እንግዲህ ምክር ቤቱ የሚመራመት የውስጥ አሰራር ስርዓት ነው፡፡

በምክር ቤቱ ውስጥ የሚገኙ አገራት የሰብአዊ መብት ጥሰት መፈፀማቸው በተጨባጭ ሲረጋገጥም ከአባልነታቸው የሚወገዱበት አሰራርም ተዘርግቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አብነት ሆኖ ሊቀርብ የምትችለው ሊቢያ ናት፡፡ ሰሞኑን በአዲስ በተተካው የሰብአዊ መብት ጥበቃ ምክር ቤት አባል ነበረች፡፡ ሆኖም የሊቢያ የተቃውሞ

ድምፅ ለመግታት ሙአመር ጋዳፊ በህዝቡ ላይ ይወስዷቸው የነበሩት እርምጃዎች የሰብአዊ መብትን የሚጥሱ ሆነው በመገኘታቸው ምክር ቤቱ ባለፈው ዓመት ሊቢያን ከአባልነት አስወግዶ ነበር፡፡ ይህም ምክር ቤት በማንኛውም መልኩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ይፈፅማሉ ለሚባሉት አገራት ቦታ እንደሌለው ያሳያል፡፡

በመሆኑም ምክር ቤቱ በሚተዳደርበት መመሪያ ላይ በሰፈረው መስፈርት መሰረት አገራት ለአባልነት ብቁ የሚሆኑት የሰብአዊ መብት ጥበቃን በማጠናከርና በማስጠበቅ ተግባር የላቀ ደረጃ ያላቸው መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው ማለት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ምክር ቤቱ ከዚህ በፊት ከነበረው ኮሚሽን በተለየ መልኩ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች አሉ የሚባሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በቅርብ የመከታተል ተግባርም የሚፈፅም በመሆኑ ጥሰቶች ያሉባቸው አገራት ከምክር ቤቱ የተደበቁ ሊሆኑ የሚችሉበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለ ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ ለመጪዎቹ ሶስት ዓመታት ምክር ቤቱን እንዲያገለግሉ ሰሞኑን የተመረጡት አገራትም ለአባልነት የበቁት እነዚህን ሂደቶች አልፈው ነው፡፡ የሚዲያ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያን ጨምሮ አርጀንቲና፣ ብራዚል፣ ኮትዲቯር፣ ኢስቶኒያ፣ ጋቦን፣ ጀርመን፣ አየርላንድ፣ ጃፓን፣ ካዛኪስታን፣ ኬንያ፣ ሞንቴኔግሮ፣ ፓኪስታን፣ የኮሪያ ሪፐብሊክ፣ ሴራሊዮን፣ ዩናይትድ አረብ ኢምሬትስ፣ አሜሪካና ቬንዙዌላ የተመረጡት በኒውዮርክ የመንግስታቱ ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት በተካሄደው ሚስጥራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ኢትዮጵያ ለተመድ የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት አባልነት የተመረጠችው ባስመዘገበቻቸው የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስኬቶችና እንዲሁም በአካባቢውና በምክር ቤቱ ምስረታ ላይ ከተጫወተቻቸው ሚናዎቿ ጋር በተያያዘ ነው ሲሉ ለአንድ የውጭ ሚዲያ መግለፃቸውን ተከታትያለሁ፡፡

ኮሚሽነሩ እንዳሉት የመንግስታቱ ድርጅት አባል አገራት ምክር ቤቱን የሚመሩት በየሶስት ዓመቱ በሚያካሄዱት ምርጫ አማካኝነት ነው፤ ኢትዮጵያም ለመመረጥ ባቀረበችው ጥያቄ መሰረት አባል መንግሥታቱ ሁኔታዋን ገምግመው በአብላጫ ድምፅ የምክር ቤቱን መቀመጫ ማግኘት ችላለች፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ የሰብአዊ መብት ጥበቃን ለማጠናከር የራሷ የሆኑ ህጎችን ከማውጣት ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀርፀው ስራ ላይ የዋሉትን ዓለም አቀፍ የፖለቲካ፣ የሲቪል፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል ስምምነቶችን ሁሉ የህጎቿ አካል አድርጋ ስራ ላይ አውላለች፡፡ የተመድ አባል አገራትም ምክር ቤቱን እንድታገለግል ሲመርጧት እነዚህን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ መሆኑን ዋና ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ገልፀዋል፡፡

ኢትዮጵያ የመንግስታቱ ድርጅት አካል የሆነው ይህ ምክር ቤት በሚቋቋምበት ሂደትም ጉልህ ሚና መጫወቷን አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እነዚሁ መረጃዎች እንደሚሉት አገሪቱ የዜጎቿን ሰበአዊ መብት ጥበቃ ለማጠናከር የራሷ የሆኑ ተቋማትን መመስረቷ የሚበረታታ ተግባር ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምንና የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋነኛዎቹ መሆናቸውም ይነገራል፡፡ ይህም ኢትዮጵያን ለምክር ቤቱ መቀመጫ ሊያበቃት እንደሚችል ብዙዎች ይገልፃሉ፡፡

የሰብአዊ መብት ጉዳይ እጅግ የተወሳሰበና በየጊዜው እየሰፋ የመሄድ ባህሪን የተላበሰ ከመሆኑ አኳያ ከሰብአዊ መብት ጋር በተያያዘ ያሉትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ በተሳካ ሁኔታ ስራ ላይ ያዋለ አገር ማግኘት ያዳግታል፡፡ ኢትዮጵያም በተመሳሳይ ከፈረመቻቸው አለምአቀፍ ስምምነቶች የሚቀሩና መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡

እነዚህ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ግን በመንግስት ሆን ተብለው የተፈጠሩ ሳይሆኑ በአፈጻጸም ሂደት ላይ ግለሰቦች ካለማወቅም ይሁን እንዲያው በቸልተኝነት የሚፈጥሩት ችግር እንደሆነ በተለያዩ ወቅቶች የወጡ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

እንዲያም ሆኖ አገሪቱ ላለፉት 20 ዓመታት የሰብአዊ መብት ጥበቃን ለማጠናከር ብዙ ርቀት ተጉዛለች ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ መንግስት የሰብአዊ መብት ጥበቃን ለማጠናከር በተጨባጭ የሚታዩ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

የኢትዮጵያን ህገ መንግስት በጥሞና ለመመርመር የሚሞክር ማንም አካል አገሪቱ ለሰብአዊ መብት ጉዳይ ከምንም ነገር የላቀ ትኩረት የምትሰጠው የግለሰቦችን ተፈጥሯዊ መብትና ፍላጎት ለማሟላት ያህል ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ ሰላምና ልማት እንደዚሁም አጠቃላይ ህልው የግድ መሆኑንም በመገንዘብ ጭምር መሆኑን በቀላሉ ይገነዘባል፡፡

አገሪቱ በ 1995 ዓም ያፀደቀችው ህገ መንግስት አጠቃላይ ይዘት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሰብአዊ መብት ጉዳይ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከባህል፣ ከእምነት፣ ከማህበራዊ ጉዳዮች ወዘተ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ህገ መንግስታችን ለሰብአዊ መብት ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል፡፡

እነዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድም የተለያዩ ፖሊሲዎች ተቀርፀዋል፤ እንደአስፈላጊነቱም ከሰብአዊ መብት ጥበቃ ጋር የተያያዘ ተግባር የሚከውኑ ተቋማትም ተመስርተዋል፡፡

የሰብአዊ መብት ጉዳይ እጅግ ሰፊና ዘርፈ ብዙ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ ጉዳይ የሚቃኘው ደግሞ ልዩ ድጋፍና ክብካቤ የሚያሻቸውን ህጻናት፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ የዜጎችን ሁለንተናዊ መብቶች ከማክበርና ከማስከበር አኳያ ይመስለኛል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በመንግስታችን በኩል ያለውን ቁርጠኝነት ለማሳየት እጅግ በርካታ አብነቶች አሉ፡፡ ህገ መንግስታችን ስራ ላይ በዋለባቸው ባለፉት ዓመታት ከዚህ ጋር በተያያዘ ብዙ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

ብዙዎቻችን እንደምናውቀው መንግስት የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞችና መሰል የህብረተሰብ ክፍሎችን መብቶችና ጥቅሞች ለማስከበር የሚያስችሉ ህጎችንና ፖሊሲዎችን የህዝብ ተሳትፎን መሰረት ባደረገ መልኩ አውጥቶ ስራ ላይ አውሏል፡፡ ይህንንም ተግባር በቅርብ የሚከታተሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶችንም አዋቅሯል፡፡ በዚህም ተጨባጭ ለውጦች በመታየት ላይ ናቸው፡፡

የዜጎችን የሰብአዊ መብቶች ያለአንዳች ሳንካ ማክበርና ማስከበር እንዲቻልም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄዱ ታላላቅ ጉባኤዎችን ተከትሎ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምና ብሄራዊ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ተቋቁመዋል፡፡ እነዚህ ተቋማትም በተለያየ መልኩ ተጥሰው የሚገኙ የዜጎች ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር የበኩላቸውን ሚና በመጫወት ላይ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱት አጠቃላይ የፖለቲካና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከሰብአዊ መብት ጉዳይ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ስለዚህም በመንግስት የሚወጡ የልማት ፖሊሲዎችም ሆኑ የተለያዩ ውሳኔዎች በምንም መልኩ የህዝቦችን ሰብአዊ መብቶች የሚጎዱ መሆን የለባቸውም፡፡

በዚህ ረገድ የመንግስትን የዘውትር የላቀ ጥንቃቄ ማንሳት ግድ ይለኛል፡፡ መንገድን ጨምሮ መንግስት ለህዝብና አገር ጥቅም ሲል በሚያካሄዳቸው የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች ሳቢያ ዜጎች እንዳይጎዱ ተገቢውን ካሳ ይከፍላል፤ የፈረሱ ቤቶች ካሉ ተለዋጭ ያቀርባል፡፡  ይህ ከሰብአዊ መብት ጥበቃ አንጻር ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ይመስለኛል፡፡

ኢትዮጵያ ከየትኛውም በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመደራጀት መብት ህገ መንግስታዊ ዋስትና ሰጥታለች፡፡ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰባሰቡባቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገሪቱ እንደአሸን ፈልተዋል፡፡ እነዚህ አካላት በህጋዊ መንገድ እየተንቀሳቀሱ የፈለጉትን የፖለቲካ አቋም በማራመድ ላይ ናቸው፡፡ የዜጎችን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ያቀዳጀው የአገሪቱ ህገ መንግስትም አያሌ ነፃ ህትመቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡

በአገሪቱ ከየትኛውም ጊዜ እጅግ በላቀ ደረጃ ለሰብአዊ መብት ጥበቃ የተሰጠው ትኩረት ዜጎች በመንግስታቸው ላይ እምነት እንዲኖራቸውና አገራቸውን እንዲወዱ እያደረጋቸው ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ለዚህም ትልቅ ማሳያ ብዬ የማምነው በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የሚታየው ከፍተኛ የኢኮኖሚ እመርታን ነው፡፡

ሰላምና መረጋጋትን ማጠናከር፣ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማምጣትና አገራዊ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የሰብአዊ መብትን ማክበር የግድ ይላል፡፡ የሰብአዊ መብቱ ያልተከበረለት ህዝብ በምንም መልኩ ከመንግስት ጎን አይሰለፍም፤ የመንግስትን ትልም በመከተልም አይተጋም፡፡

የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብቶች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብቶች መረጋገጣቸውም ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ የአገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በፌደራላዊው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት አማካኝነት የፖለቲካና ኢኮኖሚ መብቶቻቸው ተረጋግጠውላቸዋል፤ ተጠቃሚነታቸውን በተጨባጭ ማየት ጀምረዋል፡፡

ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ከአገሪቱ አጠቃላይ ኃብት ሽራፊ እንኳ የማይደርሳቸው የነበሩ የአገሪቱ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በአሁኑ ወቅት የብሄራዊ ኃብቱ እኩል ተጠቃሚ በመሆን መብታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በየክልሎቹ የሚታየውን ጤናን፣ ትምህርትንና መሰል ማህበራዊ አገልግሎቶችን ማስተዋሉ በቂ ይመስለኛል፡፡

በተለይም ቀደም ሲል መኖራቸውን እንኳ በቅጡ የማናውቃቸውን እንደ ጋምቤላ፣ ሶማሌ፣ አፋርና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ውስጥ አሁን የሚስተዋለው ለውጥ ከዚህ አኳያ ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡

በህዝብ ያላሰለሰ ትጋት የሚታይበት አገራዊ የኢኮኖሚ እድገቱም የዚሁ ነፀብራቅ ነው፡፡ የዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም በቅርኑ ይፋ ባደረገው ሪፖርቱ በአሁኑ ወቅት ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት እያሳዩ ከሚገኙት የዓለም አገራት መካከል ኢትዮጵያ ከቻይናና ህንድ ቀጥላ ሶስተኛ ደረጃ ላይ መሆኗን አረጋግጧል፡፡ እነዚህ አገራዊ ስኬቶች ለሰብአዊ መብቶት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ውርሶች ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ለሰብአዊ መብት ጉዳዮች ልዩ ትኩረትና መቆርቆር ያለው መሆኑን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከዚህ ቀደምም በአደባባይ የመሰከረው ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ እያበረከተችው ያለው ሚናም ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አገሪቱ በርስ በርስ ጦርነት ሳቢያ አፍሪካ ውስጥ የሚፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተግባራትን ለመግታት ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል ላይ ትገኛለች፡፡ በአገራቱ ሰላምና መረጋጋትን እንዲፈጥር ከማንም በላይ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተመራጭና ተአማኒ መሆን የቻለው ከዚሁ ባህሪው በመነጨ ነው ብዬ

አምናለሁ፡፡ ይህ ተሳትፎዋ በራሱ ለዚህ ምክር ቤት እንድትመረጥ የሚያበቃት ቁልፍ ተግባር ሆኖ ሊቀርብ የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም፡፡

እላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መረዳት የሚቻል አንድ ግዙፍ እውነት አለ፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያ ለሰብአዊ መብት ጥበቃ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የምትሰጥ አገር መሆኗ ነው፡፡

በመሆኑም በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላትና በአገራችን ውስጥ የመንግስትን ስልጣን እንይዛለን ብለው የተደራጁት ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ከሰብአዊ መብት ጋር በተያያዘ በየጊዜው የሚያወጧቸው የውንጀላ መግለጫዎች ፈጠራ መሆናቸውን ይኸው የምክር ቤቱ ምርጫ አረጋግጧል፡፡ ይህ ዓለም አቀፍ እውቅና እነዚህን የጥፋት መንገደኞች ፍፁም ባዶ ያስቀረ የኢትዮጵያ እውነት ነው፡፡